# በሰሜን ካሊፎርኒያ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች
# በ ሰአረ አብርሃም ሞት የተሰማን ጥልቅ ሃዘን

(በይ ኤርያ ካሊፎርኒያ) 5-27-19 - እኛ በሰሜን ካሊፎርኒያ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች በደብረማርቆስ ዩንቨርስቲ የሶስተኛ አመት ተማሪ ሰአረ አብርሃም ሞት የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እየገለፅን ለተጎጂው ወንድማችን እግዚአብሄር ነብሱን በገነት ትኖር ዘንድ ለመላው ወዳጅ ዘመዶቹ ደግሞ ፅናቱን እንመኛለን::

ይህ አረመኔያዊ ግድያ በአማራ ክልል የመጀመርያ ጊዜ አለመሆኑና ከትግራይ የመጡ ተማሪዎችን ለይተህ ማጥቃትና መግደል እንደጀብድ እየተወሰደ የክልሉ መንግስትና የተለያዩ የትምህርት ተቋም አስተዳደሮች በቂ የህግና ፀጥታ ጥበቃና ከለላ አለማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን የክልሉ ፖለትከኞች በግልፅና በስውር በሚያራግቡት ለትግራይ ህዝብ ያላቸው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እንደዋና ምክንያት መሆኑን በግልፅ ማሳወቅ እንፈልጋለን:: ገለልተኛ የሆኑ የተለያዩ የህዝብ መገናኛዎች እንደዘገቡት ከሆነ በዩኒቨርሲቲው የተከሰተው ግጭት በአማራና በኦሮሞ ተማሪዎች ቢሆንም የትግራይ ተወላጆችን ነጥሎ ግፍ በተሞላበት መንገድ መግደልና ማጥቃት የደካማነት ምልክት ነው:: ይህ ድርጊት የመላው አማራ ክልል ህዝብ እንዲያወግዘው ጥሪያችን እናቀርባለን::

በመቀጠል ይህ ኢሰብአዊ ግድያና ጥቃት በፅኑ የምናወግዘው ተግባር መሆኑን እየገለፅን በተማሪ ሰመረ አብርሃም ግድያና በሌሎች የትግራይ ተወላጆች ጥቃት የተሳተፉና ያስተባበሩ ሁሉ ለህግ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን::

በየአከባቢው እየተፈፀመ ያለው ዘር ተኮር ጥቃትና መፈናቀል በአገራችን አንድነት ያነባጠረ ስልሆነ ሁሉም አገር ወዳድ ዜጎች የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች ሊያወግዙት ይገባል:: ህግ እንዲከበር የዜጎች ጥቃት ግድያና መፈናቀል ላንዴና ለመጨረሻ እንዲቆም መንግስት የሃማኖት መሪዎችና የሃገር ሽማግሌዎች ሃላፊነታቸውን እንዲውጡ በፅኑ እንጠይቃለን::

ተጋሩ ዲያስፖራ ካውንስል ሰሜን ካሊፎርኒያ::

ግንቦት 27፣ 2019